እስቀ በቃ

ከዳኛቸው ወርቁ

«ተረት ተረት» አሉ ባለቤቷ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ዕድሜ ያለው የሚመስል አንድ ወንድ ልጅ እየተመለከቱ፡፡ ቤቱ ሬሳ የወጣበት ይመስል ጭር ብሎ ነበር፡፡

ከባንኮው በስተውስጥ ቆመዋል፤ ባለቤቷ በስተ ውጭ ፤ በጎን በኩል፣ ሁለት የሰፋነግ ትራስ ተደራርቦ እተመቻቸበት ሶፋ ሳይ አንድ ረዘም ያለ ቀጭን ሰው እግሮቹን በሰፊው አራዝሞ ተቀምጧል፡፡ የራሱ ጸጉር ከግምባሩ መካከል አንስቶ እስከ ማጅራቱ ተረተር ድረስ በቀጭኑ ተመልጧል፡፡ በረጅም መቃ ዓይነት ነገር የተሰካ ሲጃራውን፣ ባውራጣቱና በትንሽ ጣቱ መካከል አሾልኮ ፣ በሌባ ጣቱ ጫን እያ፣ ካለፍ አገደም ወደ አፉ በመውሰድ፣ የጭስ ኩቦቹን እያከታተለ ቡልቅ ቡልቅ ያደርጋል፡፡ ዓይኖቹ በር በሩን ይመለከታሉ፡፡

«ተረት ተረት» አሉ ባለቤቷ ደግመው «የሳም በረት» መለሰች አንዲቷ ቆንጆ፤ አንደዩ በብዙው አንድዩ በትንሹ ሲጃራዋን እየመጠጠች፡፡ እንደሰውዩው የጭስ ኩቦች ለመሥራት ትደክማለች፡፡ አልፎ አልፎምትን እያሳት እንደሳል ያረጋታል፡፡ በሥራው የሠለጠነው ቀጭኑ ሰውዩ የጎድን አየት እያረጋት ሳቅ ይላል፤ እያከታተለ አንድዩ በዝግታ አንዴ በፍጥነት ኩቦቹን በማስወጣት፡፡

«ተረት ተረት» አሉ ባለቤቷ ለሦስተኛ ጊዜ

«የሳም በረት» አለች መልሳ፤ ኩቦቹን ለመስራት እያተጋለች፤ ቆንጆዋ፡፡

«አንቺ አልተጠራሽም» አሉ ባለቤቷ ኮስተር ብለው

ትንሹ ልጅ እክፍሉ ውስጥ ከተኮለኮሉት ሶፋዎች መካከል ረጅሙ ሶፋ ሳይ ተቀምጦ ካርታ በመደርደር ይጫወት ነበር፡፡ ቆንጆይቱ ድንገት ብድግ ብላ መጥታ ካርታውን ከልጁ እጅ መንጭቃ ወስዳ የካርታ ጥንቆላ ጀመረች፡፡

«ምነው አስረስ ተረቱን ንገረን እንጂ» አሉ ባለቤቷ ዋጋ የሚያስከፍል በሚመስል ድምፅ፡፡

«አንድ ቤት ሁለት ውሾች ነበሩ፡፡» ጀመረ አስረስ «ቤቱ ቀዳዳ ነበር» ቀጠለ አስረስ የተነጠቀውን ካርታ እየተመለከተ «በቀዳዳው ወጡ፡፡»

«ታዲያስ» አሉ ባለቤቷ

«አለቀ በቃ» መለሰ አስረስ፡፡ ዓይኖቹ ከካርታው ሳይ አልተነቀሉም፡፡

«እሺ ፍቅርስ እንዴት ያረጋል?» ቀጠሉ ባለቤቷ፡፡

«ያስለቅሳል» አለ አስረስ እንባው እንደመጣበት ዓይነት

«ያስለቅሳል? ከየት አመጣኸው ደሞ እንዲህ ያለውን መልስ?» ከባንኮው ወደሶፋው መጥተው ቀና አርገው ዓይኑን ይመለከቱታል፡፡

«ምነው ምን ሆንክ»

«ያስለቅሳል»

«አይ ለቅሶ እዚህ የለም፣ የምን ያስለቅሳል ነው ደሞ» ይቀጥላሉ ባለቤቷ ቆጣ ባለ አንደበት፤ ወዲያው ፊቱን አበስ አበስ በማረግ «በል እንግዲህ አሁን ንገረኝ፤ ፍቅር ምን ምን ይላል?» በማለት

«ስኳር ስኳርም አይል ....ማር ማርም አይል.....»

«ጋብዙኝ» አለች ድንገት እጎኔ ተስጋ፣ ካርታ ቀሚዋ፡፡ ስትጠጋኝ አላይኋትም፡፡

« ጋብዙኝ» አለችኝ ደግማ

«ቢራ ጠጭ» አልኳት፡፡ «እሺ» አለችና ትንሽ «ጅን» ጠብ ያለበት «ቤርሙጥ» አምጥታ እጎኔ ተመልሳ ተቀመጠች፡፡ ባለኩቡ እግሩን አንጠራርቶ ባንኮው ወገብ ላይ ወግቶ በመወጠር ተዝናንቷል፡፡

«ድገሙኝ» አለችኝ፤ ስትጨልጠው አላየኋትም፡፡ ደገመች፡፡ ከሰውዬው ሲጃራ ለምና አመጣችና በመለኮስ ኩቦቹን ለመስራተ ትፍጨረጨር ጀመር እንደገና፡፡ ለኔ ለማሳየትም ይሁን ነገሩ አልገባኝም፡፡ እኔ ለራሴ የሲጃራ ሽታ ያስከረኛል፤ አልወድም፡፡ ደጉ ነገር ፈንጠር ብዬ ነበር መስኮት አጠገብ የተቀመጥኩት፡፡ የቀዩ አምፖል ብርሃን ውጋጋን ፊት ላይ በማይንተገተ ግበት በኩል፡፡ የምጠጣውም የጊዮርጊስ ቢራ ነበር፡፡

«ቆንጆ ፎርም አለኝኮ» አለችኝ ቀስ ብላ

«ጥሩ ነው» አልካት ከጪሱ በመሸሸ.

«ላሳይህ» አለችኝ

«አየሁትኮ» አልኳት

«የስም አሳየኸውም» አለችኝ

«አልገባኝም» አልኳት

«ሦስት ዊስኪ ብትገዛልኝ አሳይሃለሁ» አለችኝ፡፡

«ምን? ልብስሽን....» አልኳት ዓይኔ ሳልወድ

ጎርጬ

«አዎ ምናለበት......»

«አረ ተይ....»

«ልታይ አይደለም»

«ሁላችንም እያለን?»

«ምንድነው ለድስታችን አይደለንም....» አለች እንደሷ ዓይነት ቆንጆ ጓደኛዋን እየተመለከተች፡፡

«ታዲያ አትፈሪም?»

«ምን ታደርጉኛላችሁ? አትበሉኝ»

«በምን ታውቂያለሽ?»

«አይ ከበላችሁኝም ሕግ አለ»

«አሁን እውነት ካንጀትሽ ነው?»

በቀኝ እግሯ መሬቱን መታ መታ እያረገች፣ ሐሳቧ ርቆ የሄደ፣ ከንፈሯ ብቻ የሚንወሳቀስ በሚመስል ሁኔታ፡፡

«አይ ለውስኪው ስስተህ እንደሁ ተወው» አለችኝ

«ሰውነትሽን በመጠጣት ለመርሳት ትፈልጊያለሽን?» አልኳት፡፡

«ሳልጠጣ ሰው መሆኔን አውቀዋለሁ መቼ አልኩህ?» ስትል መለሰችልኝ፡፡

«እኔ መቼም ሰው ነሽ እላለሁ» አልኳት

«ሰው ስለሆንኩማ መጠጥ እፈልጋለሁ፡፡»

«የሰው ምልክቱ መጠጥ ነው?»

«አይ ለዊስኪው ሰስተህ እንደሁ ተወው»

«እውን አሁን ያልሽውን ታደርጊያለሽ?»

«ለምን አላደርግም»

«አይ እንዲያው አልመሰለኝም»

መልስ ከመስጠቴ በፊት ብዙ ጊዜ ቆየሁ፡፡

«አንድ መልስልህ ከፈለግህ ዊስኪውን ግዛልኝ»

«እንግዲያውስ ጠጪ» አልኳት፡፡ እንዴት እንደሄደች የምታውቀው ራሷ ናት፡፡ አንድ ግማሽ ጠርሙስ ዊስኪና አንድ ብርጭቆ ይዛ መጣች፤ ቀዳች፡፡ ባንድ ትንፋሽ ጠጣችው፡፡ ደገመች አሁንም ባንድ ትንፋሽ ጠጣችው፡፡ የነፍስ ስልክም ነፋስ እንደሆነ አላውቅም፤ እውነትም ጠምቷት ኖሯል፡፡

አየት አደረገችኝ፡፡ «ትዊስት» የሚባለው የዳንስ ሙዚቃ መሰማት ጀመረ፡፡ ከወንበሯ ላይ እያለች እንቅስቃሴዋን ጀመረች፡፡ ሦስተኛ ጊዜ ዊስኪዋን ቀዳች፡፡ ገንዘቤ መሆኑ ተሰማኝ፡፡

«ታዲያስ ተነሻ» አልኳት

የምትነጠራራም መሰለኝ፡፡ ሰው የምትጠራም መሰለኝ፡፡ ሸንጭና ዳሌዋን ጣቶቿንና ክንዷን የምታሳየንም መሰለኝ፡ አንደኛውን ጫማዋን አወለቀች፡፡ ሁለተኛውን ደገመች፡፡ ከወገቧ ጎብደድ፡ ከሸንጥና ከዳሌዋ ጎበጥ፣ ከደረትና ከትከሻዋ ቀና ባላ ግራ እጇን አራዝማ፣ በቀኝ እጇ ከግራ ከእጇ መዳፍ ጀምራ፣ ክንዷን ፣ ጡቶቿን እስከ ቀኝ ትከሻዋ ጫፍ ድረስ በቀስታ እየደባበሰች ታሪካዊ አነሣሥ አሳየች፡፡ ወደፊቷም እንደመንደርደር ብላ አንገቷን ብቻ ዘወር በማድረግ አንድ ባንድ አየችን፡፡ ቀስ እያለችም ወደ እኔ ዞረች፡፡ እጇንም በማሽቆልቆል ከቁርጭምጭሚቷ ጀምራ ባትና ጭኗን እየደባበሰች ወደ ደረቷ አመጣችው፡፡ እግረ መንገዱንም ሰውነቷን ገለጠው፡፡ የባት ጡንቻ የላትም፣ ሙላው ሙሉ ነው፡፡ እንደገና አየት አደረገችን፤ ሳቅ አይሉት ሳቅ ሳቀች፤ አስፈራችኝ፡፡ ወዲያውም«ልድገምወይ» አለችኝ ፤ ዓይን ዓይኔን እየተመለከተች፡፡ ባለኩቡ ቀድሞ ድገሚ አላት፡፡ የሚሠረው የጭስ

ኩብ ራሱ ሳይ ይትነስነሳል፡፡ እኔ ነገሩም አልገባኝ፣ እሷና እሱ ግን ተግባብተዋል፡፡ የምትደግመው፣ ያሳየችውን ትርኢት ሳይሆን ውስኪውን ኖሯል፡፡ አራተኛው ብርጭቆ ስሙ እውነትም ድጋሞሽ ከሆነ ደገመች ትርኢቱ ቀጠለ፡፡

ሶፋ ሳይ ነበር የተቀመጠኩት እግሮቼን አዝናንቼ፤ መጣች፡፡ በኋላዋ ወደ እኔ፡፡ እጭኔ ውስጥ ቀስ እያለች ገብታ ቆመች፡፡ ጭንና ጭኔን እየነካካች፡፡ ቀስ እያለችም ፊቷን ወደኔ አዞረች፡፡ እኔ አዟዟሯን ስመለከት ዱሮ ሹራቧን አውልቃለች፡፡ የት እንደወረወረችው ግን እግዜር ይወቅ፡፡

ከሳይ የለበሰችው ስስ ሸሚዝ ነው፡፡ ጉር ቀሚሷ በሰፊ ቀበቶ ታስሯል፡፡ ደረቷን ሰፋ አድርጋ ቆማ ቁልቁል ተመለከተችኝ፡፡ ከመቅጽበትም በረጃጅም ጣቶቿ ጸጉሬንና አንገቴን ስትዳብሰኝና ቀሚሷ እጫማዬ ሳይ ሲወድቅ አንድ ሆነ፡፡ ዓይኔ አብሮ ወደ ሆዴ ገባ፡፡ ቱር ብሳ ወደ ወለሉ ስትወጣ እንኳ የሚታየኝ እንደህልም ነበር፡፡ ብንን ያልኩት ብቻ እሜዳ ሳይ ሳይት ነው፡፡

ተመስገን ነው ሆኖም ታዲያ የውስጥ ልብሷን አሳወለቀችም፤ ብዙም ባይቆይ፡፡ ወደ እኔ ቀስ እያለች ተጠጋች፡፡ እንደ በፊቱ ግን አልተሞኘሁም፤ እግሬን ሰብስቢያለሁ፡፡ ምን ያረጋል እሶፋው ገሴንችና እገራ ጭኔ ሳይ ጀርባዋን ሰጥታ ተቀመጠችብኝ፡፡ የተወለወለ ነው ጀርባዋ፡፡ ጠባሳና ዥንጉርጉርነት አይታይባትም፡፡

«ቁልፉን ከኋላዬ ፍታልኝ» አለችኝ

«የምኑን» አልኳት

«የጡት መያዣየን»

«እንዴት ነው?»

«አይዞህ ንጵን ነኝ፤ ምን አስፈራህ? ጡቴን ማየት ጠሳህ እንዴ? የወደቀ መስሎህ እንደሁ» አለችኝ፡፡

«የስም ስሱ እንኳን....» ብዬ በመመለስ ፣ ራሴን ማደፋፈሪያ ነገር ልናገር ስጀምር እንደትሬንታ የሚጮህ፣ የካርታ ድርጅት ታርጋ ያለበት «ቼብሮሌት» ኦቶመቢል ወደ ነበርንበት ገደማ መጣ፡፡ ቆመ

«ታዲያ ምንድንው ፍታልኛ» አለችኝ፡፡ ልፈታ ስፈራ ስቸር ሁለት ፈረንጆችና አንድ ኢትዮጵያዊ እኛ ወዳለንበት ገቡ፡፡ ዱሮ በምታውቅበት ዘዴ ጡቷን ነቅነቅ፤ ደረቷን ሰበቅ ስታደርግ ጡት መያዛዋ ጧ ብሎ ኖሯል፡፡ ውጥርጥር ያለ ጃኬት የለበሰው አንደኛው ፈረንጅ ፊቱ ድንገት ደም ለብሶ ተንደርድሮ መጥቶ ታቅፎ ሲያሽከረክራት ሁኔታው ታየኝ፡፡

የቤቱ ውስጥ ባንዳፍታ ነፍስ ዘራ፡፡ አንዲቷ ዙሪያ ጠረ`ዛ መጥረግ፣ አንዲቷ መቀመጫ ማስተካከል፣ አንዲቷ ክንድ መጥለፍ ጀመሩ፡፡ ልጅቷን ጥርቅም አርጎ አቅፏት የነበረው ፈረንጅ ድንገት ለቀቃት፡፡ በቅጽበትም አንድ ስቴካ «ዊንስተን» ሲጃራ ከጃኬቱ ውስጥ አውጥቶ ከፍተና እቤቱ ውስጥ ሳለው ሁሉ ማደል ጀመረ፡፡ እየወረወረ፡፡ ያመለጠ

ንም ብንኖር ከመሬት አንስተንም ቢሆን ሲጃራችንን እየኪሳችን አደረግን፡፡ እኔ እንኳን አሳጨስም ነበር፤ ከማን አንሼ፤ አልተግደረደርኩም፡፡

ኩብ ሠሪው ኢትዮጵያዊ የዱሮ ባኮውን ቀደደና ሲጃራውን ተያያዘው፡፡ የሱም ተማሪ ቀደደችና ተያያዘችው፡፡ «እስቴካው» ሲጃራ አሳለቀ ኖሮ ድጋሚ ሲሰጠን ሲል፣ ባለቤቷ ከባንኮው ወጥተው ነጠቁት፡፡ «ሴሳ ባስ ሱስ ሞልቷል» ብለው፡፡ የተረፈውን በሙሉ አውጥቶ ጨመረላቸው፡፡ ኢትዮጵያዊውና አንደኛው ፈረንጅ ተመቻተው ተቀመጡና መሎቲ ቢራ ተቀዳላቸው፡፡ ጋባዣችንም ፈረንጁ ትንሽ ወዲያ ወዲህ ካ በኋላ ተቀመጠ፡፡ ግብዣዬን የተቀበለችው ወይ ዞሮ አግዜር ይስጥልኝ እንኳ ሳትል ዱሮ ሄዳ እሱው ላይ ተጠመጠመች፡፡ አጎኔ የነበረውን ወንበር ወደሪቴ አሸቀንጥሬ እግሬን እላው ላይ ዘረጋሁት፡፡ ዞርግቼ የማላውቀው ሰውዬ፡፡ ቢራዬንም ጭልጥ አደረግሁና፣ «ውስኪ ብላክ ኤንድ ሁዋይት» አልኩኝ ድምጼን ከፍ አድርጌ፡፡ ውስኪው ተቀዳልኝ፤ ባንድ ትንፋሽ ጭው አረግሁት፡፡ «ድገሚኝ» አልኳት ፡፡ ስትደግመኝ ሁለተኛው ቅጂ ተቀጣጥሎ ቁርቢል «ድቡል» አልኳት፤ ሳቅ ብላ «ድቡል» ቀዳችልኝ፡፡

«አስረስ» አሉ እመይቴ «ተረት ተረት»

«ባንድ ቤት ሁለት ውሾች ነበሩ፡፡ ቤቲ ቀዳዳ ነበር፡፡ በቀዳዳው ወጡ፡፡»

«ታዲያስ»

«አለቀ በቃ፡፡»

«ጋብዘኝ.» ትላለች የኔ ተጋባዥ፤ ታቅፏት የነበረውን ፈረንጅ እያሻሸች፡፡ ሲጃራዬን ከኪሴ መዝረጥሁት «ክብረቲት አባክሽ» አልኳት፡፡

እውጭ ስወጣ፣ አጥሩ ሥር አነበረው ቁሻሻ ውሃ መውረጃ ውስጥ ልገባ ነበር፡፡ ቀና አልኩኝ፤ አስፋ አስፋ እያለ የደመና ኩብ ይትጎለጎላል፡፡ የቤቴን መንገድ ስያያዝ ማካፋት ጀመረ፡፡